

ሚያዚያ 3 ቀን 2004 ዓ.ም.

# እንደ አንድ ሰው ሞተ¡?

(ለሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ መታሰቢያ፣ ከሊ.ማ. አ. ይግዛው)

እኔ በሕይዎቴ ከሰማሁት መርዶ፣
እንደ አፈወርቅ ያለ አላየሁም ከብዶ።
ያ ታላቁ ጠቢብ፣ የሥዕል ፈጣሪ፣
በላቀ ችሎታው፣ አገርን አስጠሪ፣
ኢትዮጵያን፣ አፍሪካን፣ በዓለም ያኮራ፣
ድንገት ሞተ ሲባል፣ በየትም ሲወራ፣
የበጋ መብረቅ ነው፣ በጣም የሚያስፈራ።

በአነጋገሩ፣ ለዛው የሚያስደንቅ፣
ግርማ ሞገስ ያለው፣ ሰው ነበር አፈወርቅ።
አፈወርቅ ተክሌ በኢትዮጵያ ሲኖር፣
አፉ ብቻ አይደለም፤ እጁም ወርቅ ነበር።
ለሙያው፣ ለክብሩ፣ ኢያወላውሌ፣
አንጋፈው ሠዓሊ ሜትር አፈወርቅ ተክሌ፣
እንዴት ተሠበረ እንደ ስስ ብርሌ!?
በኢትዮጵያ፣ ብሎም በአፍሪካ፣
ይህን ታላቅ አርቲስት፣ ማን ነው የሚተካ¡?
በራሱ ዘይቤ እየተራቀቀ፣
በንድፉ፣ በቅቡ፣ ከሁሉም የላቀ፣
በሥዕል ቅላፄ ሁሉን ያስደነቀ፣
ያን ያህል ተሰጥዎ፣ ጥበብ ያካበተ፣
አፈወርቅ ተክሌ በሕማማት ሞተ?
ሜትር አፈወርቅ ተክሌ፣ እንደ አንድ ሰው ሞተ?
ከእግዜር ቀጥሎ፣ በፈጠራ ሥራ፣
ባርአያው፣ በመልኩ፣ ፍጥረትን የገራ፣
ከአፈወርቅ እኩል ማን ነው የሚጠራ?
የእርሱ ሞት ለሀገር ከባድ ነው መከራ።
ስሙን ችሎታውን፣ በውል የሚያስጠራ፣
በሚገባው ስፍራ መዘክር ይሠራ።
እማማ ኢትዮጵያ፣ እግዚአብሔር ያጥናሽ፣
እማማ የሚልሽ ልጅሽ ሞተብሽ።



እማማ ኢትዮጵያ